የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከሚያዚያ 22 እስከ 29፣ 2017 ዓ.ም
APRIL 30 - MAY 7/2025 G.C

1. ኢትዮጵያ የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነትን በቅርቡ መተግበር ትጀምራለች-ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፤ሚያዝያ 27/2017(ኢዜአ)፦ኢትዮጵያ የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነትን በቅርቡ መተግበር ትጀምራለች ሲሉ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) ገለጹ።
የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) ሳምንትን አስመልክቶ ሁለተኛው የኮሜሳ ተቋማዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፎረም በአዲስ አበባ መካሄድ ጀምሯል።
የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) ሳምንትን አስመልክቶ ሁለተኛው የኮሜሳ ተቋማዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፎረም በአዲስ አበባ መካሄድ ጀምሯል።

ኢትዮጵያ የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ አባል ከሆነች ከሃያ ዓመታት በላይ ቢቆጠሩም የገበያው ተጠቃሚ እንዳልነበረችም ነው ያስታወሱት።
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባለፈው ሐሙስ ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ለአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት የዕቃዎች ቀረጥ ምጣኔ ቅነሳን ለማስፈፀም በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቷል።
በአባል አገሮች መካከል የሚደረጉ ግብይቶች በታሪፍ ምክንያት ሳይደናቀፉ የእቃዎች ፍሰት የተሳለጠ እንዲሆን ከአባል አገሮች በሚመጡ እቃዎች ላይ የጉምሩክ ታሪፍ ምጣኔ ለይቶ መወሰን አስፈላጊ መሆኑንም ጠቅሰዋል።
ምክር ቤቱ ደንቡ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተፈፃሚ እንዲሆን በሙሉ ድምጽ መወሰኑን ተከትሎ ከጥቂት ቀናት በኋላ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነትን መተግበር ትጀምራለች ብለዋል።
እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ኢትዮጵያ ለአህጉሪቷ የንግድ ውህደት እያደረገች ባለው አስተዋጽኦ የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) ሳምንትን እንድታዘጋጅ ተመርጣለች።
አገሪቷ በግብርና፣በማዕድንና በቱሪዝም ዘርፉ እምቅ አቅሞቿን በመጠቀም በገበያው ያላትን ድርሻ ለማስፋት የሚያስችላት መሆኑንም አመልክተዋል።
ሃያ አንዱ የኮሜሳ አባል አገሮች በኢትዮጵያ እየታየ ያለውን ሁለንተናዊ ለውጥ እንዲረዱ ጉብኝትን ጨምሮ የተለያዩ የፓናል ውይይቶች መዘጋጀታቸውን ነው ያመለከቱት።
ሃያ አንዱ የኮሜሳ አባል አገሮች በኢትዮጵያ እየታየ ያለውን ሁለንተናዊ ለውጥ እንዲረዱ ጉብኝትን ጨምሮ የተለያዩ የፓናል ውይይቶች መዘጋጀታቸውን ነው ያመለከቱት።
የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) ዋና ፀኃፊ ቺሌስ ካፕዌ፤ ለአየር ንብረት ተፅዕኖ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት የፈጠራ ስራዎችን ማጠናከር እንደሚገባ ጠቅሰው፤ለንግድ ሥራ ፈጣሪዎች ተገቢው ድጋፍ ሊደረግ እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ የሴቶች ቢዝነስ ፌዴሬሽን ሰብሳቢ ማውረን ሱምቤ፤ ሴት ስራ ፈጣሪዎች ያላቸውን አቅም አውጥተው እንዲጠቀሙ ዕድሉን ማመቻቸት ይገባል ብለዋል።
ኮሜሳ ሴቶችን በቴክኖሎጂ በማብቃትና ተጠቃሚ በማድረግ የገበያ እድል እንዲመቻችላቸው እያደረገ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) ሳምንት "የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም የግብርና፣ ማዕድን እና ቱሪዝም የእሴት ሰንሰለቶችን በማጎልበት ክልላዊ ውህደትን ማፋጠን" በሚል መሪ ሀሳብ በተያዩ ሁነቶች ይከበራል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_6537884

2. የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ምርቶችን ተወዳዳሪነት አሳድጓል-አምባሳደር ግርማ ብሩ

አዲስ አበባ፤ሚያዝያ 27/2017(ኢዜአ)፦የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ምርቶች ተወዳዳሪነት እንዲጨምር ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪ አምባሳደር ግርማ ብሩ ገለጹ።
ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) 3ኛውን የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ በአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል በይፋ መክፈታቸው ይታወቃል።
የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪ አምባሳደር ግርማ ብሩ እና የኮሙዩኒኬሽን ሚኒስትሩ ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) እንዲሁም የሚኒስቴሩ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ኤክስፖውን ጎብኝተዋል።
ጉብኝቱን አስመልክቶ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪ አምባሳደር ግርማ ብሩ በሰጡት ማብራሪያ፥ ኢትዮጵያ ታምርት የሀገር ውስጥ ምርታማነት እንዲጨምር ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል ብለዋል።
የኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ለማጉላት በመንግስት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ውጤት እያመጡ መሆናቸውን በኤክስፖው መመልከታቸውንም ተናግረዋል።
ዘርፉ ያለበትን የፋይናንስና መሰል ችግሮችን በመቅረፍ ረገድ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከቱንም አክለዋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በዋናነት ትኩረት ካደረገባቸው ዘርፎች መካከል የኢንዱስትሪ ምርታማነትን መጨመር አንዱ መሆኑን ያብራሩት አማካሪው፥ በዚህም አበረታች ውጤት መመዝገብ ተችሏል ነው ያሉት።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_6539518

3. የኢትዮጵያ የሥጋ ምርት በዓለም አቀፍ ገበያ ተመራጭ እንዲሆን ለማስቻል እየተሠራ ነው

አዲስ አበባ፣ ሚያዝያ 24፣ 2017 (ኤፍ ኤም ሲ) የኢትዮጵያ የሥጋ ምርት ቻይናን ጨምሮ በዓለም ዓቀፍ ገበያ ተመራጭ እንዲሆን ለማስቻል ከቻይና ጋር በትብብር የሚሰራው ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገልጿል።

በደቡብ ደቡብ ትብብር በተለያዩ ዘርፎች ትብብራቸውን ያሳደጉት ኢትዮጵያ እና ቻይና የእንሥሣትን ምርታማነትን ለማሣደግ የሚያሥችሉ ሥራዎችን ጨምሮ የተለያዩ ተግባራትን በትብብር እያከናወኑ እንደሆነ ተመላክቷል።

የኢትዮጵያን ከፍተኛ የእንሥሣት ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ትኩረት አድርጎ የሚሰራው የእንሥሣት ምርት እሴት ሰንሰለት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ሁለተኛ ምዕራፍ ፕሮጀክት ዛሬ ይፋ ሆኗል።

በሥነ ሥርዓቱ ላይ በግብርና ሚኒስቴር የእንሥሣት ሀብት ልማት አማካሪ አለማየሁ መኮንን (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ በዘርፉ የሁለቱ ሀገራት ትብብር እየተጠናከረ መጥቷል።

ኢትዮጵያ የምግብ ሉዓላዊነቷን ለማረጋገጥ እየሠራች በምትገኘው ሥራም የእንሥሣት ሀብቷን በአግባቡ እየተጠቀመች እንደምትገኝ ገልጸዋል።

https://www.fanamc.com/archives/291674

በውጭ ቋንቋ(English)

4. IMF Slashes Sub-Saharan Africa's Growth Forecast for 2025

Reporter: April 26/2025

The International Monetary Fund (IMF) has revised its economic growth forecast for Sub-Saharan Africa, downgrading its October 2024 prediction of 4.2 percent to 3.8 percent for 2025.

The revision reflects a range of challenging economic conditions, including weaker external demand, plummeted commodity prices, and tighter financial markets.

"We now expect growth in Sub-Saharan Africa to ease to 3.8 percent in 2025 and 4.2 percent in 2026, down from October's projections," said Abebe Aemro Selassie, director of the IMF's African Department. "This adjustment is driven largely by the global economic environment, with weaker demand from abroad, lower commodity prices, and tighter financial markets."

During a press briefing at the 2025 IMF and World Bank Spring Meetings in Washington, DC, on Friday, Abebe explained that the growth forecast for 2025 has been cut in line with a downward shift in the global economic outlook.

"Regional growth is expected to slow this year due to these external challenges," he stated.

He also warned that further trade tensions or tightening financial conditions in advanced economies could dampen regional confidence, raise borrowing costs, and delay investment decisions.

https://www.thereporterethiopia.com/44858/

5. Ethiopia and Regional Economic Integration: Challenges and Opportunities

Capital: April 7, 2025

Regional economic integration (REI) is the process by which neighboring countries come together to form economic alliances that enhance trade, investment, and overall economic cooperation. These agreements reduce or eliminate trade barriers, streamline regulations, and foster stronger economic ties between member nations.

Regional economic integration takes various forms, depending on the depth of economic cooperation among member nations. These forms include the following: Free Trade Area (FTA): Member countries agree to eliminate tariffs and trade restrictions among themselves while maintaining individual trade policies with non-member countries. Examples include the North American Free Trade Agreement (NAFTA, now USMCA) and the European Free Trade Association (EFTA).

Customs Union: In addition to eliminating internal trade barriers, member states adopt a common external tariff on imports from non-member countries. The Southern Common Market (MERCOSUR) is an example.

Common Market: This level goes beyond a customs union by allowing the free movement of labor, capital, and services among member states. The European Economic Area (EEA) is a good example.

Economic Union: In this integration form, member nations not only share trade policies but also coordinate economic policies, including monetary and fiscal policies. The European Union (EU) is the most notable example.

Political Union: The highest level of integration, where member nations unify their economic, political, and social policies under a single governing authority. The EU has some characteristics of a political union, though full political integration has not been achieved.

Ethiopia, as one of the largest economies in East Africa, plays a significant role in regional economic integration efforts. Given its strategic location, growing economy, and infrastructural developments, Ethiopia has actively participated in various regional economic communities (RECs) to foster trade, investment, and economic cooperation. However, several challenges continue to hinder its full integration into the regional economy. This article explores Ethiopia's role in regional economic integration, the benefits it seeks, and the challenges it faces.

https://capitalethiopia.com/2025/04/07/